# በ‹‹ቀሺም ሲሚንቶ›› ለተገነባ ቤት ተጠያቂው ማነው?

**ሚስባህ**

**09-01-14**

የቀሺም ሲሚንቶን ነገር የሰማሁት ፕሮፌሰር መሥፍን ወልደማርያም ሰሞኑን በሸገር ኤፍኤም 102.1 ጨዋታ ፕሮግራም ላይ የ97ቱን ቅንጅት በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ ነው፡፡ "የሦስት ፓርቲዎች ጥምረት የነበረውን ቅንጅት መበታተን ተከትሎ በምራቅ የተጣበቀ ስለነበር ነው" ሲሉ ለነበሩ ወገኖች አስተያየትዎ ምንድነው? ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ ፕሮፌሰሩ ሲመልሱ ከምራቁ ሳይርቁ ፓርቲዎቹ እንደ ፓርቲ ሊዋሃዱም ሆነ ሊቀናጁ ይችሉበት ዘንድ አስፈላጊ የፖለቲካና የፖለቲካ ፕሮግራም እንዲሁም ርዕዮተ አለማዊ ግብአቶች ሳይመጣጠኑና ሳይሟሉ ስለምርጫ ብቻ ሲሉ መዋሃዳቸው በቀሺም ሲሚንቶ እንደተገነባ ቤት ሳይውሉ ሳያድሩ ይፈርሱ ዘንድ ግድ ብሏቸዋል አሉ፡፡

የዚህ የቀሺም ሲሚንቶ ጉዳይ አሁንም የቀጠለ መሆኑን የመኢአድንና የአንድነትን ሰሞንኛ የውህደት ከበሮ በመጥቀስም ነካ አድርገዋል፡፡ እናም ጉዳዩ በእርግጥም ትክክል መሆኑ ለዚህ ፅሁፌ መነሻ ሆነኝ፡፡ መቼም ሁሉም ነገር እንደየባህሪው እና እንደየአፈጣጠሩ ሥርዓትና ሙያ፣ ባለሙያና ባለቤት፣ ተጠያቂና ጠያቂ እንዳለው ግልፅ ነው፡፡ አንድ ቤት ሊያስገነባ ያሰበ ግለሰብ እንደ አሰሪና ባለቤት ለፈለገው የቤት አይነትና መጠን አስፈላጊ የሆኑ ግብአቶችን ማሟላት የግዱ ነው፡፡ የቀረበውን ግብአት በንድፍ ባለሙያው በቀረበው ፕላን  መሰረት አዋህዶ እና መጥኖ በንድፍ ባለሙያው ቤቱ እንዲሆንና እንዲቆይ በሚያስችለው ደረጃ መስራት ደግሞ የተቋራጩ ሚና ነው፡፡

ከዚህ ውጪ አንዳቸውስ እንኳ የራሳቸውን ሚና ቢዘነጉ እና ያለቦታቸው ቢገቡና ቢወቅጡ የቤቱ ዕድሜ ላይ፤ አልያም ደግሞ ጥራት ላይ አንዳች እክል መፈጠሩ አይቀሬ ነው፡፡ አሰሪው ወይም ባለቤቱ የፈለገውን አይነት ቤት እንዲገነባለት በባለሙያዎቹ የቀረበለትን ግብአት ሳያሟላ ቢጠብቅም ከንቱ ነው፡፡ ቢያንስ ምክር ቢለግሱት አልሰማ ቢልና በዚህ አግባብ ብቻ ይሰራልኝ ብሎ ሙጭጭ ቢል ያቀረበው ግብአትና የተፈለገው ቤት አይመጣጠኑምና መደርመሱ አይቀሬ ነው፡፡

በዚህ ጊዜ ዋና ተጠያቂ የሚሆነው ደግሞ ራሱ አልሰማ ያለው ባለቤት ነው፡፡ ነገር ግን ለደረሰው ጥፋት ጣቱን የንድፍ ባሙያው ላይ አልያም ተቋራጩ ላይ ቢቀስር አስቀድሞ ተነግሮት ነበርና፤ ጉዳዩም የምህንድስና ሳይንስ እንጂ በአሰሪ ፍላጎት አይለካምና አሰሪ የሻተውን ለማግኘትም የተጠየቀውን ሊያሟላ ግዱ ነበርና ባላሟላበት አግባብ ውስጥ፤ ሊገጥመው የሚችለው ችግር አስቀድሞ ተገልፆለታልና ዋና ተጠያቂ ከመሆን እንዴትስ ሊድን ይቻለዋል?

በሀገሬ የሚገኙ የተቃዋሚ ፓርቲዎችም በቀሺም ሲሚንቶ እንደተገነባው ቤት ባላቀረቡት ግብአትና መጥነው ባልደቆሱት ያልተሰራ ፖለቲካ ሲፈርሱና ሲፈረካከሱ ጣታቸውን ወደሌላ የመቀሰርና ይልቁንም የፓርቲዎች የመጫወቻ ሜዳውን ባዘጋጀው መንግስትና ጨዋታውን በህግ አግባብ በሚመራው የምርጫ ቦርድ ላይ ማላከክ የተለመደና የነበረ ሲሆን ለመጪውም ምርጫ ይህንኑ የከሰረ ስትራቴጂ ሊቀጥሉበት እያቆበቆቡ ይመስላል፡፡ ይህን ለማረጋገጥም ፕሮፌሰር ነካ ወዳደረጉትና መጪውን ሃገር አቀፍ ምርጫ ታሳቢ በማድረግ በቀሺም ሲሚንቶ እየተዋሃደ ያለውን የመኢአድና የአንድነት ሰሞነኛ ጉዳይ በቅጡ መመልከት ተገቢ ነው፡፡

የእነዚህ ደግሞ የሚከፋው በቀሺም ሲሚንቶ እየተዋሃዱ መሆኑን እያወቁትና፤ አውቀውም እየነገሩን ሲያበቁ በቀሽም ሲሚንቶ በመገንባት ላይ ናቸውና መፈራረሳቸው የጊዜ ጉዳይ እንጂ አይቀሬ መሆኑንም ተገንዝበው ሳለ፤ የፈረሱ እንደሁ የቀሺሙን ሲሚንቶ ባለቤት ባልተቀጠረበት እና ኮንትራቱን ባልተጫረበት አግባብ ኢህአዴግ ላይ ለመለጠፍ የማቆብቆባቸው ጉዳይ ነው፡፡

ይህ ደግሞ በቀሺም ሲሚንቶ ለተገነባው ቤት ተዋናይ እንደነበሩት ግንበኛና አናጢዎች የመኢአድና የአንድነትን ውህደት ግንበኛና አናጢ በመሆን ስለቀረበላቸው ዱልዱም ሚስማር ፣ ጠማማ እንጨትና ቀሺም ሲሚንቶ ከመሞገት ይልቅ በጉልበትና በግርግር ብቻ ለማዋሃድና ለመገንባት በመዞር ላይ ከሚገኙ የፕሬስ ውጤቶች ማረጋገጥ ቢያንስ "ከካድሬ"ፍረጃ ያድነናል፡፡ በአናቱም አንባቢያንንም ሆነ በስሙ የሚማልበትን ህዝብም ከጥርጣሬ ይታደጋል፡፡

የ97ቱ ቅንጅት ከፍተኛ አመራር የነበሩት ፕሮፌሰር መሥፍን በወቅቱ ባይናገሩትም ይልቁንም ለቅንጅቱ መበታተን እና መፈረካከስ ምክንያቱ "ገዢው ፓርቲ ነው" ሲሉ

ጣታቸውን ቀስረው የነበረ ቢሆንም ቆይተው ሲገነዘቡና ሲረዱት የቅንጅቱ መፈረካከስ ምክንያቱ በቀሺም ሲሚንቶ  የተገነባ ስለሆነ መሆኑን ሲናገሩ ተደምጠዋል፡፡ ልክ እንደእርሳቸው አሁን በውህደት ሂደት ላይ ከሚገኙት መኢአድና አንድነት በአባሎቻቸውና ከፍተኛ እንደሆኑ በሚነገርላቸው አመራሮቻቸው የቀሺም ሲሚንቶዋ ነገር ተመልሳ የመምጣቷን ነገር በግልፅ እያመኑና እየተናገሩ፤ ሲሚንቶውም ቀሺምና የፖለቲካ ሳይንሱ ከሚፈቅደው አግባብ ውጪ ናቸውና መፈራረሳቸው እንደማይቀር ቢገምቱም ምክንያቱን ኢህአዴግ ላይ ለማላከክ እየተንደረደሩ ነው። ያም ሆኖ ግን ወደ ኋላ ማመናቸው አይቀሬ ነውና ከወዲሁ ብናሳስባቸውና ብንጠቁማቸው አንድም እየተዋሃዱ ያሉት እና እየማሉ የሚገኙት በስማችን ነውና ሁለትም ግንባታውም ለእኛው መኖሪያ ነው ተብለናልና ተገቢነት ይኖረዋል፡፡ ለዚህ ጉዳይ ብቁና ሁነኛ ማሳያ የሚሆነኝ ደግሞ ከውህደቱ ባለቤት አንዱና የአንድነቱ ከፍተኛ አመራር የሆኑ ግለሰብ ከግንባታው ባለሙያዎች አንዷ በሆነችው ፋክት መፅሄት ላይ ያስቀመጡልን ያልተመጠነና በበቂ ግብአት ያልተሟላ ፕሮፌሰር ለሽገሩ የጫወታ ፕሮግራም እንዳሉት የውሃ ቅዳ ውሃ መልስ  ጨዋታ ነው፡፡

አብዛኞቹ ፀሐፊዎችና የፓርቲዎቹ አባላት የአንድነትን እና የመኢአድን ቅድመ ውህደት ስምምነት ልክ እንዳለቀለትና ያበቃለት ውህደት ወስደው ሲያበቁ ትችታቸው ውህደቱ የሚፀናበት ጉዳይ ላይ ይመስላል፡፡ በፋክት መፅሄት ቁጥር 58 በነሀሴ 2006 መፅሄት ላይ ”2007ን ለምርጫ ወይስ ለዴሞክራሲያዊ መንግስት” በሚል ትርክታቸውን ያሰፈሩትና የአንድነት ፓርቲ ከፍተኛ አመራር የሆኑት ግለሰብም፤ ወጋቸውን የሚያሟሹቱ በዚህና የቅድመ ውህደት ስምምነቱን ያበቃለት ውህደት እንደሆነ (የእሳቸው እምነት ቢሆንም እኛም እንድናምን) በሚሞግት መንገድ ነው፡፡ እሳቸውንም የሚጨምር እንደሆነ ከወጋቸው አጠቃላይ ይዘት መገንዘብ ቢቻልም የተቃውሞ ፖለቲካውን በቅርበት የሚከታተሉ ግለሰቦች አስተያየት እንደሆነ በመጥቀስ ”የህውደቱ መሳካት አዎንታዊ ጎን ቢኖረውም ዘግይቷል፡፡

በዚህ ጊዜ የውህደቱ ጣጣ አልቆ፣ የሚተባበሩት ተባብረው ወደሰፊ ህዝባዊ ንቅናቄ የሚገቡበት ነበር፡፡” በማለት ገልጸዋል፡፡ ለእኛ ቁልፍ ጥያቄ የሆነው ጉዳያችን የእርሳቸውም እንደሆነ በሚያሳብቅ መልኩ፡፡ ”የውህደቱ መሳካት ጥሩ ሆኖ ውህደቱም ሆነ ትብብሩ ዘለቄታ ያለው ዴሞክራሲያዊ ለውጥ ለማምጣት ወይስ ምርጫ ስለደረሰ ብቻ? የሚል ጥያቄ አንስቶ መመለስ ተገቢ ነው" ይሉናል፡፡ በእርግጥ ጥያቄው የእኛም መሆኑ

እንተደጠበቀ  ሆኖ ግን ደግሞ  ውህደቱ ግና መቼ ተሳካና ነው የውህደቱ መሳካት ጥሩ ሆኖ ሳለ…በሚል መንገድ የተንደረደሩት? ስንል ፀሃፊውን መልሰን ለመጠየቅ እንገደዳለን፡፡

ፀሃፊው በትርክታቸው ላይ እንዳሰፈሩልን ለዚህ ትርክታቸው መነሻ የሆናቸው ፓርቲዎችን በተመለከተ በተለይም የተቃዋውን ጎራ ውህደት በተመለከተ ከአንድ ጓደኛቸው ጋር ያደረጉት ውይይት ነው፡፡ ይልቁንም ጓዳቸው ይህን ወግ የጀመረላቸው እኔም ከፍ ብሎ እንዳመለከትኩት ፀሃፊው ለተቃዋሚ ፓርቲዎች ቅርበት እንዳላቸው ስላመነ መሆኑን ነግረውናል፡፡

ስለሆነም የፀሃፊው ጓድ ስለተቃዋሚ ፓርቲዎች ቁመና ለፀሃፊው ያወሩላቸውንና ፀሀፊውም የጓዳቸው ሀሳብ እንደሆነ በትርክታቸው ላይ ያሰፈሩት ነጥብ ፓርቲዎች የሚገለፁበትና ስለውህደትና የተቃውሞ ፖለቲካ ያላቸውን ምልከታ የሚያረጋግጥ ነውና እኛም መልሰን ብናሰፍረውና ብናጤነው ተገቢ ነው፡፡

‹‹በተቃውሞ ጎራው በኩል ተቀራርቦ፣ ተባብሮና ተዋህዶ የመስራቱ ነገር እምብዛም ባለመለመዱ ወይም እስካሁን ባለመሳካቱ ይመስለኛል፣ ውህደቱ እንደ አንድ አደረጃጀትን የሚያጠነክር የፖለቲካ ስራ ሳይሆን፣ እንደ ግብ ይታያል፡፡ ከፖለቲካ ጠቀሜታ አንፃር ሳይሆን ከምርጫ ከግል ጥቅምና ዝና አንፃር ይታያል፡፡ ውህደት እንደ አንድ የለውጥ ማምለጫ ስልት ባለመታየቱ በህዝቡ ዘንድ በጉጉት የሚጠበቅ ነው፡፡ መጠላለፍና ሴራ በብርቱ የሚያጠቃው የፖለቲካ ባህላችን ግን "**እኔ ብቻ አዋቂ  እኔ ብቻ ንጉስ**" **ከሚል ጨፍላቂ ስርዓት ጋር** ሲደመር ግራ ማጋበቱ ላይገርም ይችላል፡፡ በአጠቃላይም የተቃውሞ ጎራውን ከአሮጌና ምርጫን ግብ ካደረገ አስተሳሰብ አላቅቀው፣ የራሱ መነሻና መድረሻ ያለው ስልት የሚነድፉ መሪዎች ያስፈልጉታል" ብሎ የፀሃፊው ጓድ አላበቃም። ይህንንም አከለ፡፡

"ለነገሩ መምራት የሚችሉ ግለሰቦች ለመምጣት ቢሞክሩም በጥርጣሬና በሴራ ፖለቲካ ተስተካካይ የሌላቸው ግለሰቦች እንዲርቁ ያደርጓቸዋል፡፡ ከእነርሱ የተረፉትን ደግሞ ኢህአዴግ "አሸባሪ" ብሎ ያስራቸዋል፡፡ ስለዚህ ውህደት ብቻ ሳይሆን ውህደቱን የሚመራ ብቁ መሪ ያስፈልጋል፡፡ ምርጫ ሞክሮ የሚሄድ ሳይሆን ከምርጫ ባሻገርም ለውጥ

የሚመጣበትን መንገድ የሚቀይስ ብርቱ ሰው" በማለት ሀሳቡን መጠቅለሉን ፀሀፊው ተርከውልናል፡፡

እንግዲህ ያው እንደተለመደው ሁሉም ማለት ይቻላል የተቃዋሚውን ፖለቲካ ቡድን ሲያሂስ ለምን እንደሁ እና ማሂሱ ካልቀረ ሊያስተምራቸው ሲገባ "ችግራችሁ ከእናንተ ብቻ የሚመነጭ ሳይሆን ከኢህአዴግም ነው" ማለትን አዘውትረው ለምደው አስለምደዋቸዋልና እነርሱም ሌባ በቀደደው መንገድ ገብተው ከራሳቸው ወደ ኢህአዴግ ማላከክን መልመዳቸው በግልፅ እየታየ ነው፡፡

ከላይ በተመለከተው ርዕስ ፋክት ላይ የተቃውሞውን እና የነመኢአድን ውህደት በተመለከተ ያስነበቡን እና ለፅሁፋቸውም መነሻ ከሆናቸው የጓዳቸው ምልከታ በተመለከትነው ነጥብ፣ ከተቃዋሚዎቹ ካምፕ የምንሻውና እንደ ፓርቲም የሚጠበቅባቸው በርካታ ፖለቲካዊ ስራዎች መኖራቸው በሚገባ ተጠቅሶ ስለጉድለታቸው ኢህአዴግም "እኔ ብቻ አዋቂ" በሚልና የ"አሸባሪነትን" ታርጋ ለጣፊ ተደርጎ በምክንያት ቀርቧል፡፡ ኢህአዴግ የ"አሸባሪነት" ታርጋ እየለጠፈና "እኔ ብቻ አዋቂ" እያለ ጨፍላቂ መሆን አለመሆኑን እራሱ ይመልስ፡፡ እኛ ደግሞ ዝም ብለን ኢህአዴግ "ከኔ በላይ ላሳር" የተጠናወተው ጨፍላቂና የአሸባሪን ታርጋ በመለጠፍ አሳሪ ነው ብለን እንቀበልና፡፡ የአሸባሪነትን ታርጋ እየለጠፈና ከእኔ በላይ ላሳር የጨፍላቂነት ባህሪውን ትቶ ሁሉን ነገር አልጋ በአልጋ አደረገም እንበልና በፀሃፊው ለጽሁፉ መነሻ የሆነው ጓዱም ሆነ ፕሮፌሰር መሥፍን ለሸገሩ የጫወታ ፕሮግራም እንዳወሱት ተቃዋሚዎቹ አልጋ በአልጋ በሆነበትና ምህዳሩ በተበንቦረቀቀበትም የፖለቲካ አውድ ውስጥ እንደ ተቃዋሚ ፓርቲ ተደራጅተው ዴሞክራሲያዊ ሥርዓተ መንግስት ለመመስረት የሚያስችል አቋም አላቸው ወይ? ብለን መጠየቅና መልሱንም ከዚሁ ኢህአዴግንም እንደ ምክንያት ከጠቀሰው የፀሃፊው ጓድ ምልከታ ላይ እንውሰድ፡፡

ተቃዋሚዎቹ ውህደትን አንደ አንድ አደረጃጀትን የሚያጠናክር የፖለቲካ ስራ ሳይሆን ከሳይንሱ አፈንግጠው እንደግብ ማየታቸው፣ የውህደት ቁምነገሩ የፖለቲካ ጠቀሜታው መሆኑ የፖለቲካው ሳይንስ ሀሁ ሆኖ ሳለ የኛዎቹ ደግሞ ከምርጫ፣ ከግል ጥቅምና ዝና አንፃር ማየታቸው፣ ውህደት የለውጥ ማምጫ ስልት መሆኑን መዘንጋታቸው፤ መጠላለፍና ሴራ የሚያጠቃቸው ስብስቦች መሆናቸው፤ ጎራውን ከአሮጌውና ምርጫን ግብ ካደረገ አስተሳሰብ አላቆ የራሱ መነሻና መድረሻ ያለው ስልት የሚነድፉ መሪዎች የሌሉት

መሆኑ፤ ሲመጡም በጥርጣሬና በሴራ ፖለቲካ ተስተካካይ የሌላቸው ግለሰቦች እንዲርቁ በሚያደርጓቸው ውስብስባም ግለሰቦች የተሞላ ካምፕ መሆኑ ወዘተ በራሱ የገዘፈ ሸክም ሆኖ ሳለ ኢህአዴግን እንደምክንያት ማንሳት እንዴት ይቻላል?

በምርጫ 97 ወቅትም የሆነው ይኸው እንደነበር ፕሮፌሰር ለጨዋታ ፕሮግራም ሲያወሱ፤ ስብስቡ የለውጥ መሳሪያ መሆን ሳይሆን የለውጥ ባለቤት መሆንን የሚሻ፣ በስልጣን ጥም የናወዘ በመሆኑ እና ምርጫውንም ከራሱ ፍላጎት አኳያ በመቃኘት "በቀሽም ሲሚንቶ" መጣበቁ ሳይቆይ እንዲፈረካከስ ግድ ያለው መሆኑን በማስታወስ ነው፡፡ በወቅቱ ተቃዋሚዎቹ ይህ ሁሉ ጀንያ የሚሞላ የፖለቲካ ሸክም ይዘው የኢህአዴግን ጥቃቅን ችግሮች እንደምክንያት ሊያሂሱ ቢሞክሩም እንደ ፕሮፌሰር ገለፃ ኢህአዴግ በወቅቱ በቃኝ ብሎ እንኳ ቢለቅና ሰበብም ቢጠፉ ተቃዋዎቹ በአንድነት ሃገር ሊረከቡ የማይቻላቸው እንደነበር በበርካታ ማሳያዎች አጢነናል፡፡

አሁንም ማሳያ ባዳረግነው የፋክት መፅሄት ላይ ከሰፈረው ትርክት የወሰድናቸው ተቃዋሚዎቹን የተመለከቱ ነጥቦች (ይሁን ብለን እንኳ ብንወስድ) ከኢህዴግ "ከእኔ በላይ ላሳር ትምክህትና በአሸባሪነት የመፈረጅ ሴራ" የሚልቁ እና ሊወራረዱ የማይችሉ በመሆኑ የእናቴ መቀነት ጠለፈኝን ተውት ብለን እናሳስባለን፡፡ አሁን ደግሞ ውህደቱን 2007ን ከምርጫና ከዴሞክራሲያዊ መንግስት አኳያ በ"2007ን ለምርጫ ወይስ ለዴሞክራሲያዊ መንግስት" በሚለው ትርክቱ ወደቃኘው የአንድነቱ ከፍተኛ አመራር ተሻግረን ወሳኝ የሆኑትን ነጥቦች እንምዘዝ፡፡

በእርግጥ ይህም ትርክት ኢህአዴግ ላይ (መለመዱን ከላይ ገልፀነዋልና) ማላከኩ ባይቀርም፤ ግን ደግሞ ከላይ በተመለከተው ምዘናችን አግባብ (ይሁን እንኳ ብለን ብንቀበል) የተላከከበት አካልና የማላከኪያው ምክንያት ከካምፑ በርከት ያሉ ኩንታል ችግሮች አኳያ ኢምንት መሆኑን እንደወረደ አስፍረን በማየት ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ የልጅነት ጨዋታቸውን ማሄስ እንችላለን፡፡

ጓዱን መነሻ አድርጎ ከላይ በተመለከለተው ርዕስ ለተጠቀሰው ፅሁፍ እና የተቃዋሚውን ጎራ ለተመለከተው አስተያየት "ጋንግስተሪዝም" የሚል ርዕስ ሰጥቶታል፡፡ እናም እንዲህ ሲል ጎራውን ይገልፀዋል፡፡ "ጋንግስተሪዝም (ቦዘኔነት) ዋናው የተቃዋሚ ጎራ ችግርም ነው፡፡ ቦዘኔዎች ዋና ተግባራቸው ስራ መስራት አይደለም፡፡ የሚሰሩትን እየተከታተሉ

ማጥቃት እንጂ …" የሃሳብ ልዩነትን በውይይት ከመፍታት ይልቅ ማጥፋት የተለመደ ነው፡፡ በተቃዋሚው ጎራም አባራሪና ተባባሪ አለ፡፡ "የተቃዋሚዎች እናት አንድ ናት" እንዲል አሥራት አብርሃም …ፕሮፌሰር መሥፍን እንዳሉት የሥላሴዎች እርግማን ይሆንን? አደህይቶ መግዛት፣ አጎሳቁሎ ተስፋ ማሳጣት፣ ባዶ ማድረግ፣ ጋንግስትሪዝም፡፡"

ፀሃፊው ያው እንደለመደው ኢህአዴግንም ተጠያቂ ማድረግ መገለጫው ስለሆነው የተቃውሞ ካምፕ እንዲህ ይቀጥላል…፡፡ "ይህ ሊሆን የሚችለው (ዴሞክራሲያዊ መንግስት ለማለት ነው) ደግሞ ምርጫ ስለደረሰ ሱፋቸውን አሳምረውና ጫማቸውን ወልውለው ከተቻለ ፓርላማ፣ ካልተቻለ ደግሞ ሌላ አምስት አመት እስከሚመጣ ቤታቸው በሚቀመጡ ፖለቲከኞች አይደለም፡፡"

ይህ እንግዲህ የተቃውሞው ካምፕን በተመለከተ ጋንግስተሪዝም ከሚለው የፀሃፊው ሃሳብ ከተገለፀበት ትርክት የተቀነጨበ ነው፡፡ ግና ካምፑን በተመለከተ ከምርጫ 2007 ጋር ተያይዞ የሰፈረው ትርክት አላበቃም፡፡ "የምርጫ ጊዜ ወፎች" በሚል ንዑስ ርዕስም ይቀጥላል፡፡

"… የእነዚህ ወፎች ግብ ከላይ እንደገለፅኩት ዘለቄታዊ ለውጥ በማምጣት የሚፈለገውን ዴሞክራሲ መገንባት አይደለም፡፡ **ዘላቂነት ያለው የለውጥ ስሜትም ሆነ ስትራቴጂ ስለሌላቸው፣** በምርጫ ጊዜ ብቻ ብቅ ይሉና "ሲያቃጥል በማንኪያ ከበረደ በእጅ" የምትል የጮሌ ስትራቴጂ በመያዝ ምርጫ ላይ ለመሳተፍ የሚፈልጉት ናቸው፡፡

እነዚህ ሃይሎች ከረባት በማሳመር ምርጫ ማሸነፍ ይቻል ይመስል "**የ2007ን ምርጫም መሞከር አለብን"** ይላሉ፡፡ መሞከር ብሎ ትግል ግን ምን ይሆን?! ሰው የሚወዳደረው ለመሞከር ሳይሆን ለማሸነፍ ነው፡፡ የምርጫ ጊዜ ወፎች ግን "ኧረ እባካችሁ ህዝብና ሀገር መሞከሪያ አይደለም፤ **ኢህአዴግ በዚህ ጭቁን ህዝብ ላይ የሞከረበት ይበቃል፣ ዘላቂነት ያለው ስትራቴጂና ራዕይ ካላችሁ ወዲህ በሉ"** ሲባሉ ያኮርፋሉ፡፡ ይፈርጃሉ፡፡ ያችኑ የሚያውቋትን የሴራ ጨዋታ ከች ያደርጓታል፡፡ ያ የፈረደበት ምርጫ 97 ይጠቀስና "ስንት ዋጋ ከፍለን፣ ደማችን ፈሶ፣ አጥንታችን ተከስክሶ…" የምትል "ፉከራ" በማምጣት ጉዞ ወደ ምርጫ ሙከራ ይሆናል፡፡

… ዳሩ ግን **ከታሪክ መማር እንጂ በታሪክ መኖር አይቻልም፤ በታሪክ መስራት እንጂ በታሪክ ማሸነፍ አይቻልም፡፡** ማሸነፍ የሚቻለው **ዛሬ ላይ አቅዶ፣ እቅዱን ወደተግባር**

*ለውጦ ህዝን አሳትፎ መጓዝ ሲቻል ብቻ ነው፡፡"* አሁን ወደ ፀሃፊው የመደምደሚያ ምልከታ ደርሰናል፡፡ *"የግል ይዞታነት"* የሚል ንዑስ ርእስም ለመደምደሚያ ሃሳቡ ሰጥቶታል፡፡"... አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ከምርጫ ባለፈ የምንመለከት ከሆነ በተቃዋሚ ጎራው የሚታየውን *ፓርቲን እንደ ግል ንብረት የመመልከትን ዝንባሌ ማጥራት ያስፈልጋል፡፡* በትግል ውስጥ ዋጋ መክፈል ማለት ፓርቲውን እንደግል ንብረት ማድረግ ማለት አይደለም፡፡ ... እኔ አይነኬ ነኝ" የሚሉ አንዳንድ ግለሰቦች "እኔ እንደዚህ፣ እንደዚህ አድርጌ በመሰረትኩት ፓርቲ..." የምትል መከራከሪያ ሲያቀርቡ ይሰማል፡፡ ፓርቲ ውስጥና ፖለቲካ ውስጥ *"እኔ"* የምትል የግለኝነት ሃሳብ መነሳት ከጀመረች፣ ህዝብና ሃገር ተዘንግቷል ማለት ነው፡፡... ማንም ሰው ማወቅ የሚገባው ወደ ኢትዮጵያ የተቃውሞ ፖለቲካ *የሚመጣው ሊሰጥ እንጂ ሊቀበል እንዳልሆነ ነው፡፡*

አሁን ኢህአዴግ ላይ የቀረቡ ማመሃኛ ነጥቦችን (በዚህ ትርክት የተጠቀሱትን ብቻ ሳይሆን ሁሌም የሚሰሙትን) ጨምረን የተቃውሞውን ካምፕ በተመለከተ በተለይ የተሰመረባቸውን ነጥቦች እንመልከትና ሃሳቡን እናወራርድ፡፡ ኢህአዴግ ምህዳሩን ያጥብብም፣ ይሰርና ይፍታ፤ እንደፓርቲ ፓርቲ ሆኖ እቅድ ከሌለው ስትራቴጂና አደረጃጀት የማይታወቅ ከሆነበት፣ እኔ አይነኬ ነኝ የሚሉና ፓርቲን እንደግል ንብረታቸው የሚመለከቱ ስብስቦች ካሉበት አንድነትና መኢአድ በቅንጅት መንፈስ እንሰራለን እንዳላሉ ከታሪክ መማር እንጂ መኖር አይቻልምና እንዲሉ ማሳያ ፀሃፊያችን፣ በከረባት ለማሸነፍ በምርጫ ወቅት ብቅ በሚሉ ስብስቦች የታጨቁበት ካምፕ ምንስ ቢደረግ፤ ምህዳሩ ከሚፈልጉትም በላይ ቢንቦረቀቅ ሚዲያው ሁሉ ተጠቅልሎ ቢሰጣቸው፤ ገንዘብም እንዳለ ቢቸራቸው እርስ በእርስ ሊጠላለፉበት ሊሰዳደቡበት እና ሊዘባበቱበት ካልሆነ ምንስ ሊያደርጉት ይችላሉ? ሊቀበል እንጂ ሊሰጥ ዝግጁነት ከሌለው ስብስብ፤ በሴራ ፖለቲካ ጠምዶ ማባረርንና መባረርን የለመደ ስብስብ የፈለገውን ክስ ቢያሰማ መጀመሪያውኑ በሁለት እግሩ አልቆመምና ማን ሊሰማው ሽቶ ይሆን? ቀደም ብዬ የገለፅኩት ለዚህ ፅሁፍ ማሳያ የሆነን ተራኪያችን ጓድ ለፀሃፊው የተናገራትን አንዲት ነገር እዚህች ጋር  እናስታውስ፡፡

"አየህ ተቃዋሚው በአጠቃላይ ከአፈጣጠሩ ጀምሮ በርካታ ችግሮች ያሉበት ነው" ኢህአዴግ የሚፈጥረው ችግር ደግሞ ብዙ ነው፡፡ ላለፉት 23 ዓመታት ተቃዋሚው በተበታተበነ አሰላላፍ፣ ምርጫን ብቸኛ ግብ አድርጎ ቆይቷል፡፡ ይህ አሰላለፍ ዘላቂነት ላለው ድልና የማይናድ የተቃውሞ ግንብ ለመገንባት አላስቻለውም፡፡ ግልፅ ራዕይና

ስትራቴጂ በማስቀመጥ፣ ተተኪ ፖለቲከኞችን በማፍራትና በውስጡ ተሰግስገው እንደ አሜባ የሚራቡትን ሰርጎ ገቦች ለማጥራት አልቻለም… ወዘተ፡፡”

የኢህአዴግ ችግር በፀጉራቸውም ልክ ቢሆን ግልፅ ራዕይ ሳይኖራቸው ግልፅ ስትራቴጂ ሳይዙና ግባቸውን ከፖለቲካው መርህ ባሻገር ለሆነ የምርጫ ጊዜ ግርግር ካደረጉ ፓርቲዎች ኢህአዴግን ድራሹን ብናጠፋላቸው እንኳ ምን ሊያደርጉን ይቻላቸው ይሆን? ፕሮፌሰር የሥላሴዎች እርግማን እንዲሉ ሲል…ተራኪያችን እንዳለን ፕሮፌሰር በቀሺም ሲሚንቶ የተጣበቀውን ቅንጅት አውስተው በእርሱ መንፈስ ሊኖሩ የሚዋትቱትን መኢአድና አንድነት ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ እንዲሉ  በዚህ ማሳያ አድርገን በወሰድነውና የአንድነቱ ከፍተኛ አመራር በሆነው ፀሃፊ ዘንድ የአንድነቱን እና መኢአድን ውህደት በመስጋት ምክር አዘል ድቆሳ አቅርቦ ሌሎቹን ”የምርጫ ጊዜ ወፎች” እንደሆኑ በገደምዳሜ ቢገልፃቸውም፤ አስቀድሞም በመግቢያዬ እንዳመለከትኩት ውህደቱ ያላበቃ እንደነበር ተዘንግቶ የተዘረዘረው ዲስኩር ይህን ፅሁፍ እስክጨርስ እንኳ አላደርስ ብሎ ፕሮፌሰር ***በቀሺም ሲሚንቶ*** ብለው የለውጥ መሳሪያነት የለውጥ ባለቤት ለመሆን ያሰፈሰፈውን ሃይል እንደገለፁልን፤ ፀሃፊውም በታሪክ መኖር አይቻልም ብሏልና፤ በታሪክ ለመኖር አቆብቁበው የነበሩትና ሳይጣመዱ ተጣምደናል ሲሉ የተኮፈሱቱ ሁሉ ይኸው ልክ ሳጠናቅቅ የእነርሱም ሲሚንቶ በአንድ ቀን ፀሀይ ተበልቶ አለቀና መፋታታቸውን አወጁ፡፡ ስለሆነም  ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ እና ከላይ የተመለከቱ የጓዳቸውን ሂስ ማየትና ማስተካከል እንጂ ኢህአዴግ ላይ በማላከክ እንኳንስ ለመስራት ለመቆዘም የሚሆንም ፋታ አያስገኝምና ይኸው ጨዋታው ፈረሰ ዳቦው ተቆረሰ፡፡

የአንድነት ምክር ቤት ውስጡ በተፈጠረው ሽኩቻና የሴራ ፖለቲካ ማን ካለእኔ ከሚሉና በታሪክ በሚቆዝሙ አመራሮች ተፅእኖ በሚመሰል መልኩ ውህደቱን ስለ ማዘግየቱ የፓርቲዎቹን ሊቀመናብርቶች ምንጭ ካደረገው የሸገር ኤፍኤም ዜናም ይህን ጽሁፍ በማሰናዳት ላይ ሳለሁ ሰማሁ፡፡

ስለሆነም ያልኩት ሁሉ ትክክል መሆኑን አረጋገጥኩ፡፡ ጨቋኝ የሚሉትን ኢህአዴግ፤ ጨፍላቂ የሚሉትን ኢህአዴግ በቡልዶዘር ብናስወግድላቸውም ግና **እነርሱ ሊቀበሉ እንጂ ሊሰጡ አልታደሉምና በቀሺም ሲሚንቶ ተጣብቀዋልና** እንኳስ ለህዝብ ለራሳቸው እንኳ ውለው ስለማደራቸው እርግጠኛ አንሆንም፤ ለምን? ቢሉ ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ መገለጫቸው ነውና፡፡

እንኳንስ መኢአድና አንድነት ሊዋሃዱ ይቅርና አሁን የሁለቱም ቤት የውህደቱን አመራሮች በተመለከተ ሽኩቻው አስቀድሞ ተፈጥሮ ነበርና፤ በዚህም መነሻ በቡድን የተከፋፈለው ሃይል እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል አባዜ የባህሪው ነውና፤ እኔም ካላገኘሁ ሁለታችንም ይቅርብንን መርጦ ውህደቱን አዘግይቷልና፡፡

ቅንጅትም ሲበታተን እንዲሁ ነበርና፤ አሁን ምርጫ 2007 ሳይደርስ ከምላሴ ፀጉር ይነቀል ስል እነግራችኋለሁ አንድነት በራሱ ብዙ ቦታ ሲበታተን ማየታችሁ አይቀሬ ነው፡፡ ያኔም **ኢህአዴግ ነው** የበተነን ቢሉ ምላሻችሁ ከላይ ከተመለከቱት ማጠየቂያ ነጥቦች አኳያ እንደሚሆን አያጠራጥርም፡፡